

# ማናለብሽ ፡ ነጋ ።

1950 ፡ ዓ.ም. ፡ – ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ።

## Mannallebsh Negga

1958 — 2024 A.D.

# ያ፯ ፡ መታሰቢያ ።

# In Memoriam

መስከረም ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፳፻፲፯ ፡ ዓ.ም. ።

# ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ።


## ዐጪር ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ።

ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡ ከአባታቸው ፡ ከሊ. ፡ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ እና ፡ ከእናታቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ በዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ በ 1950 ፡ ዓ.ም. ፡ ተወለዱ ።



ዐዲስ ፡ አበባ ፡ በሚገኘው ፡ "ሊሴ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ትምህርት ፡ ቤት" ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርታቸውን ፡ አጠናቅቀው ፥ የኹለተኛ ፡ ደረጃቸውን ፡ እንዳጋመሱ ፥ በ 1964 ፡ ዓ.ም. ፥ አባታቸው ፡ ሊ. ፡ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴነት ፡ ከባልተቤታቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ ልጆቻቸውን ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ መግሪብ ፡ ሲኼዱ ፥ ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፥ በመግሪብ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ሪባጥ ፡ በሚገኘው ፡ "ሊሴ ፡ ዴካርት" ፡ የኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርታቸውን ፡ አገባደዱ ።

በ 1967 ፡ ዓ.ም. ፥ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ ፈርሶ ፡ በጊዜያዊው ፡ ወታደራዊ ፡ ደርግ ፡ ሲተካ ፥ ሊ. ፡ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ዐዲሱን ፡ አስተዳደር ፡ በመቃወም ፥ ከመላ ፡ ቤተሰብ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ ተሰደዱ ። ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋም ፡ እለንደን ፡ በሚገኘው ፡ በ"ሊሴ ፡ ሻርል ፡ ደ ፡ ጎል" ፡ የኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርታቸውን ፡ ለኹለት ፡ ዓመታት ፡ ቀጥለው ፥ ወደ ፡ "ዩኒቨርስቲ" ፡ መግቢያ ፡ "ባካሎሬያ"ቸውን ፡ በማግኘት ፡ ወደ ፡ ፍራንስ ፡ ተሻገሩ ። በ"ናንሲ ፡ ዩኒቨርስቲ" ፡ እና ፡ በ"ሶርቦን ፡ ዩኒቨርስቲ" ፡ በታሪክ ፡ የ"ቢ.ኤ." ፡ ዲግሪያቸውን ፡ አግኝተው ፡ በ 1977 ፡ ዓ.ም. ፡ ወደ ፡ ለንደን ፡ ተመለሱ ። ከዚያም ፥ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ ተቀጥረው ፡ እስከ ፡ 1984 ፡ ዓ.ም. ፡ ሲሠሩ ፡ ቈዩ ።




በ 1984 ፡ ዓ.ም. ፡ ከሚስተር ፡ ሮድኔ ፡ ዌብስተር ፡ ጋራ ፡ ትዳር ፡ መሥርተው ፡ በ"ኢስት-ሳሴክስ" ፡ መኖር ፡ ዠመሩ ። ከባለቤታቸው ፡ ጋራም ፡ Concrete Innovation and Design የተሠኘ ፡ ድርጅትን ፡ አቋቁመው ፡ ለሰባት ፡ ዓመታት ፡ ከሠሩ ፡ በኋላ ፥ ለትምህርት ፡ ከነበራቸው ፡ ታላቅ ፡ ፍቅር ፡ የተነሣ ፥ በ 1991 ፡ ዓ.ም. ፥ ወደ ፡ "ዩኒበርስቲ" ፡ ተመልሰው ፥ ከሥራቸው ፡ ጋራ ፡ የሥነ ፡ ሕይወት ፡ (የ"ባዮሎጂ") ፡ ትምህርታቸውን ፡ በ"ኢስት-ሳሴክስ ፡ ዩኒቨርስቲ" ፡ ለሦስት ፡ ዓመታት ፡ ተከታትለው ፥ የ BSc. ፡ ዲግሪያቸውን ፡ አገኙ ።

እስከ ፡ 2004 ፡ ዓ.ም. ፡ ድረስ ፡ በዚያው ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ መሥራታቸውን ፡ ቀጥለው ፥ በ 2004 ፡ ዓ.ም. ፥ ከድርጅቱ ፡ ተለይተው ፥ በ"ሀውዚንግ ፡ አሶሲዬሽን" ፡ ውስጥ ፡ በዘርፍ ፡ ኀላፊነት ፡ ላ 4 ፡ ዓመታት ፡ ከሠሩ ፡ በኋላ ፥ በ 2008 ፡ ዓ.ም. ፡ "ናሽናል ፡ ሄልዝ ፡ ሰርቪስ" ፡ ውስጥ ፡ በሒሳብ ፡ ሠራተኛነት ፡ ለ 6 ፡ ዓመታት ፡ አገለገሉ ።

በዚህ ፡ ኹሉ ፡ የስደት ፡ ዘመን ፥ የሚወዷት ፡ ሀገራቸው ፡ ኢትዮጵያን ፡ የማገልገል ፡ ጽኑ ፡ ፍላጎት ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፥ በተቻላቸው ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ቅን ፡ ተሳታፊ ፡ ነበሩ ። በግላቸው ፡ ደግሞ ፥ በውጭ ፡ ሀገር ፡ ተወልደው ፡ የሚያድጉ ፡ ሕፃናት ፡ ዐማርኛ ፡ መናገር ፡ እና ፡ ባማርኛ ፡ መጻፍ ፡ የሚማሩባቸውን ፡ ዘዴዎች ፡ እየፈጠሩ ፡ አበርክተዋል ። በተለይ ፡ በ 1990 ዎቹ ፡ ያሳተሙት ፡ የፊደል ፡ እና ፡ የንባብ ፡ መማሪያ ፡ ሥዕላዊ ፡ መጸሐፍ ፥ እንዲሁም ፡ "ግጥምጥሞሽ" ፡ ብለው ፡ የሰመዩት ፡ ሕፃናትን ፡ እያጫወተ ፡ ፊደልን ፡ የሚያስተምር ፡ Puzzle ፡ ጕልሕ ፡ ማስረጃዎች ፡ ናቸው ።

መጨረሻውን ፥ በ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ ላይ ፥ ዕድሜያቸው ፡ ለጡረታ ፡ መቃረቡን ፡ ተገንዝበው ፥ ቀሪውን ፡ ሕይወታቸውን ፡ በውድ ፡ ሀገራቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ለመጨረስ ፡ ዐቅደው ፥ ከለንደን ፡ ወደ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ እየተመላለሱ ፥ ሽግግራቸውን ፡ በሚያጠናቅቁበት ፡ ወቅት ፥ ድንገተኛ ፡ ሕመም ፡ አግኝቷቸው ፥ ለሦስት ፡ ቀናት ፡ በለንደን ፡ "ሴንት ፡ ጆርጅ" ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ሲታከሙ ፡ ቈይተው ፥ ሐምሌ ፡ 10 ፡ ቀን ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ፥ በተወለዱ ፡ በ 66 ኛ ፡ ዓመታቸው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በዕረፍት ፡ ተለይተዋል ።

ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፥ ፈገግታ ፡ የማይለያቸው ፡ ፍልቅልቅ ፥ እጅግ ፡ ደግ ፣ ርኅርኅት ፡ እና ፡ ቸር ፡ ልጃችን ፡ እና ፡ እኅታችን ፡ ነበሩ ። ሰውን ፡ ማስደሰት ፡ የሚወዱ ፥ የተቸገረን ፡ ለመርዳት ፡ ዘወትር ፡ የሚጨነቁ ፥ ፍቅራቸውን ፡ በተግባር ፡ የሚያሳዩ ፥ ፍጹም ፡ ታማኝ ፡ እና ፡ ቁም ፡ ነገራም ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ነበሩ ።

ድንገት ፡ በመጣ ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ መለየታቸው ፡ ለቤተሰቦቻቸው ፡ እና ፡ ለወዳጆቻቸው ፥ ለሚያውቋቸውም ፡ ኹሉ ፥ እጅግ ፡ አስደንጋጭ ፡ እና ፡ አሳዛኝ ፡ ድርስ ፡ ኾኗል ።

ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገነተ ፡ ማርያምን ፡ ነፍስ ፡ በዐጸደ ፡ ገነት ፡ ከደጋጎች ፡ ጐን ፡ ያኑርልን ።

የወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡ ቤተሰብ ።



ጊዜው ፡ ቀዘቀዘ ፥  በረደ ፡ ቤታችን ፤
ባንቺ ፡ ተነሽና ፥  እንኪድ ፡ አገራችን ።

ናፈቅሽኝ ፡ ባንቺዬ ፤  ቀረብኝ ፡ ልማዴ ፤
መተኛት ፡ አቃተኝ ፡ እየባባ ፡ ሆዴ ።

ባንቺ ፡ ኼደች ፡ ዐሉኝ ፡ በረዥሙ ፡ መንገድ ፤
ከንግዴህ ፡ አላያት ፡ ባቋራጭም ፡ ብኼድ ።

ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

ባንቹ ፥
እግዚአብሔር ፡ እጥሩ ፡ ቦታ ፡ ያሳርፍሽ ።

ገበያነሽ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

ሚኒዬ !

ኹሉ ፡ ባንቺ ፣  ባንቺ ፣  ባንቺዬ ፡ እያለሽ ፥
ሚኒ ፣  የኔ ፡ ሚኒ ፣  ሚኒዬ ፡ ስልሽ ፡
በቀልድ ፡ በጨዋታ ፥
አሣቀሽ ፣  ወደድሽው ፣  ኾነልኝ ፡ ስምሽ ፤
የኔ ፡ አቻም ፡ የለሽ ፡ የኔ ፡ ወደር ፡ የለሽ ፡
የኔ ፡ ማናለብሽ ።



ናፍቆት ፡ በርትቶብን ፡ ተቃጥረን ፡ ነበረ ፥
መጥቼ ፡ እስክስምሽ ፡ ቸኵዬም ፡ ነበረ ፥
ጊዜው ፡ ዐልፎ ፡ ኖሮ ፡ ሳይኾንልን ፡ ቀረ ።

ተቃጥረን ፡ ነበረ ፡ ሮብ ፡ ለት ፡ ልመጣ ፥
ገባሽ ፡ ዐሉ ፡ እሐኪም ፡ ቤት ፡ እሑድ ፡ ወደ ፡ ማታ ።
ከተኛሽው ፡ እንቅልፍ ፡ ልቀሰቅስሽ ፡
ሚኒ ፣  የኔ ፡ ሚኒ ፣  ሚኒዬ ፡ ብዬ ፡ ብጠራሽ ፥
ምነው ፡ አልነቃ ፡ ዐልሽኝ ፧  አለልማድሽ ።
ምን ፡ ኾንሽ ፡ ሚኒዬ ፥  ምነው ፡ ዝም ፡ ዐልሽ ፡ ዛሬ ፧
መጥቻለኹ ፡ እኮ ፡ ፈጥኜ ፡ በርሬ ።

ሚኒ ፣  የኔ ፡ ሚኒ ፣ ሚኒዬ ፡ የኔ ፡ እናት ፥
ምነው ፡ ሳትነግሪኝ ፡ አርገሽው ፡ ሚስጥር ፥
ምነው ፡ ሳንማከር ፡ ሳንነጋገር ፥
ቈርጠሽ ፡ መነሣትሽን ፡ መኼድሽን ፡ የምር ፧

ትንሿን ፡ እኅቴን ፡ የታናሼን ፡ ታናሽ ፡
ዐጣኹት ፡ ሚኒዬን ፥  ኼደችብኝ ፡ በጧት ።
ኧረ! ፈልጉልኝ ፥  አምጡልኝ ፡ ይዛችኹ ፥
ታላቅ ፡ ነው ፡ ቀዳሚ ፡ ብላችኹ ፡ ነግራችኹ ።

ድልወንበራ ፡ ነጋ ።

ውድ ፡ እኅታችን ፣ ዐብሮ ፡ አደጋችን ፣ ጓደኛችን ፡ ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡ (ባንቹዬ) ፤ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳንጠብቀው ፡ በድንገት ፡ ማረፏ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሐዘን ፡ ጭኖብናል ። ስለ ፡ ባንቹዬ ፡ ያለን ፡ በፍቅር ፡ የታነጸ ፡ ትዝታ ፤ ጊዜ ፡ የማይሽረው ፡ የማይቀይረው ፡ ነው ።

ከኹሉም ፡ የማይረሳን ፤ የነበራት ፡ ሣቅ ፣ ደስታ ፣ ጨዋታ ፡ እና ፡ ቀልዷ ፡ ለኹሉም ፡ ጊዜ ፡ ከልባችን ፡ ሳይወጣ ፡ ለዘላለም ፡ ይኖራል ።

ቸር ፡ አምላክ ፡ ለቤተሰብ ፡ በሙሉ ፡ ብርታትን ፡ ይስጥልን ፤ የባንቹዬንም ፡ ነፍስ ፡ ይማርልን ።

ዳጨው ፡ መርዕድ ፣
ደብሪቱ ፡ መርዕድ ፣
ሙኒት ፡ መርዕድ ።



ባንቺዬ ።

መቼ ፡ ልትመጣ ፡ ነው ፡ ባንቺ ፡ ዐዲሳባ ፧
ባንቺ ፡ ኼደች ፡ ዐሉኝ ፡ በሐምሌ ፡ ጨለማ ፤
ዳግም ፡ ላትመለስ ፡ ድምፇን ፡ ሳታሰማ ፥
ኧረ ፡ ለማን ፡ ልጩኽ ፡ ማንስ ፡ ቢሰማ ።
አገር ፡ በመግባቷ ፡ እጅግ ፡ ተደስታ ፤
ምን ፡ ነካብኝ ፡ ባንቺን ፤ ቀረች ፡ ሳትመጣ ።
ባንቺዬ ፡ እመጣለኹ ፡ ብላኝ ፡ በመስከረም ፤
መንገዷን ፡ ለወጠች ፡ ኼደች ፡ ለዘላለም ።
ተሸክሜው ፡ ልኑር ፡ እሳቱን ፡ በሆዴ ፤
ባንቹዬ ፡ ነበረች ፡ የኔ ፡ መድኀኒቴ ።
ዐብረን ፡ ያቀድነውን ፡ ዐፈር ፡ አለበስሽው ፥
ምነው ፡ ሳትነግሪኝ ፡ ብቻሽን ፡ ወሰንሽው ፧
ባንቺዬ ፡ ትልቋ ፤ የኔ ፡ ቁም ፡ ነገር ፤
እንዴት ፡ ብዬ ፡ ዛሬ ፡ ነበረች ፡ ልበል ፧
ማናለብሽ ፡ ነጋ ፤ ባንቺውላ ፡ ማርያም ፤
እንገናኛለን ፡ እወዲያኛው ፡ ዓለም ።

ብርሃኔ ፡ ነጋ ።



## የሐዘን ፡ እንጉርጉሮ ።

ስደትም ፡ መለየት ፥ ሞትም ፡ መለየት ፡ ነው ፤
መራራውን ፡ መንገድ ፡ መምረጥሽ ፡ ለምን ፡ ነው ፧
ካንድ ፡ ግንድ ፡ ካንድ ፡ ሐረግ ፡ ተፈጥረን ፡ ስንኖር ፤
በዐይነ ፡ ሥጋ ፡ በአካል ፡ ሳንተያይ ፡ ቀረን ።
ታሪክም ፡ ቢጠና ፥ ሥነ ፡ ሕይወት ፡ ጭምር ፤
ሊያስቀርሽ ፡ አልቻለም ፡ ከኼድሽበት ፡ ሀገር ።
ዕውቀትና ፡ ሐሳብ ፡ ታበዛ ፡ ነበረ ፤
ልጆች ፡ ለማስተማር ፡ ትታትር ፡ ነበረ ፤
ይህ ፡ ልፋት ፡ ዐላማ ፡ ድንገት ፡ ተሰበረ ።
ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡
ኼደች ፡ አባቷጋ ።

መሰለ ፡ ማሞ ፡ አሽኔ ፤
ናዝሬት ፡ (አዳማ) ፥
ኢትዮጵያ ።

ማናለብሽ ፡ ነበር ፡ ስም ፡ ሲያወጡ ፡ አባቷ ፤
*"እኔ ፡ አለኹኝ!"* ፡ ብሎ ፡ ሞት ፡ ቆመ ፡ ከፊቷ ።
ሰው ፡ መውደድሽን ፡ ሰምቼ ፡ ብመጣ ፡ ፍለጋ ፥
አቋርጠሽ ፡ ኼድሽ ፡ ዐሉኝ ፥ ማናለብሽ ፡ ነጋ ።
ስላላገኘኹሽ ፡ ተመለስኩ ፡ እቤቴ ፤
እስከምንገናኝ ፡ ይመችሽ ፡ እኅቴ ።

ታፈሰች ፡ ማሞ ፡ አሽኔ ።



ሕይወት ፡ … ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፨
እንደ ፡ ዋዛ ፨
ታይቶ ፡ እንደሚጠፋ ፡ ጤዛ ፨
እንደ ፡ ማለዳ ፡ እንፋሎት ፡
ተኖ ፡ እንደሚያልቀው ፡ በቅጽበት ።
ባንቹዬ ፡ ባወቅንሽ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜያት ፡
ብዙ ፡ ነበርሽ ፥
ደግ ፡ ነበርሽ ፥
መካሪ ፡ ነበርሽ ፥
ፀጋ ፡ ብዙ ፡ ነበርሽ ።
የቅጽበት ፡ ፈገግታሽ ፡ እንደማለዳ ፡ ብርሃን ፡
እየፈካ ፡ እንደሚሄደው ፥
ነፍስን ፡ አጥንትን ፡ እንደሚያለመልመው ።
መስሎን ፡ የሚቈየን ፡
አሻግሮ ፡ ክረምትን ፥
አጥብቶ ፡ መስከረምን ፥
ዘመድ ፡ አዝማድን ፡ አሰባስቦ ፥
የጠፋብንን ፡ ወግ ፣ ሣቅ ፣ ጨዋታ ፡
መልሶ ።
እንገናኝ ፡ መስሎን ፥
ትተሽልን ፡ ኼድሽ ፡ ትዝታሽን ፥
ሰው ፡ መውደድሽን ፣ መፈለግ ፡
ማክበርሽን ።
ምነው ፡ ባላወቅንሽ ፥ ምነው ፡ በላየንሽ ፥
ለምደነውም ፡ አልነበር?
ብቸኝነቱን ፥
በሰው ፡ ተከቦ ፡ ያለሰው ፡ መኖርን ፥
እንኖረውስ ፡ አልነበር?
የአልባስጥሮስ ፡ ሽታ ፡ ገፈታትሮን ፥
ከሰው ፡ ሽታ ፡ ነጥሎን ።
እውይ ፡ ሐምሌ ፡ ይብሱን ፡ ጨለመ ፤
ፈገግታዋን ፡ ይዞብን ፡ ታበሰ ።
ግን ፡ ኹሌም ፡ ትኖሪያለሽ ፡ በእኛ ፡ ቤት ፥
አስረሽናልና ፡ በፍቅርሽ ፡ በረከት ።

ነፍስሽ ፡ በሰላም ፡ ትረፍ ፡ ባንቹዬ ።

ሐምሌ ፡ 12 ፡ ቀን ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ፡ ተጻፈ ፥
ከለማ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ቤተሰብ ።

ውዶቼ ፥
በብዙ ፡ እንባና ፡ ፍቅር ፡
ይህቺን ፡ ልኬያለኹ ።

አመመኝ ፡ አመመኝ!
ነጋ ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ ሳየው ፡ ወጋገኑን ፥
ማናለብሽ ፡ ስትኼድ ፡ ዳግም ፡ ጨለመብን ።
ባንቹ!
እንደ ፡ ጠዋት ፡ ጀምበር ፡ ሀገር ፡ ቤት ፡
ተገልጠሽ ፥
ሩጫሽን ፡ ጨረሽ ፡ እንግልጣር ፡ ላይ ፡
ጠለቅሽ ።
እናንት ፡ መጻተኞች ፡ ወንድም ፡ እኅቶቼ ፥
ሕመሙ ፡ መጥናቱ ፡ እንደው ፡ እስከመቼ ፨
ለማን ፨ ብዬ ፡ ነበር ፡ ዝምታን ፡
መምረጤ ፥
ፈገግታው ፡ እያለኝ ፡ ረመጠ ፡ ውስጤ ።
ተስፋ ፡ አለኝ!
ጊዜ ፡ ይመጣና ፡ ሸክሙ ፡ ሲቀለን ፥
ባንድ ፡ ላይ ፡ ኹላችን ፡
እንገናኛለን ፥ ከፈይ ፡ ተሸልመን ።

ኤልያስ ፡ ለማ ።



Bantchyé, ma jeune sœur.

Ton beau sourire et ta joie à mon mariage en 2011 resteront à vie dans ma mémoire.
Bantchyé, ta présence avec Mammitou avait tellement ensoleillé et égayé la maison à Rabat, au Maroc, ton second pays.
Toute la famille marocaine se souvient de ces moments agréables que nous avons passé ensemble depuis l'arrivée de notre famille Negga au Maroc.
Quels ne furent ma douleur et mon chagrin d'apprendre par Mammitou au téléphone ton départ soudain auprès de Dieu.
Tu resteras dans mon cœur jusqu'à mon dernier souffle ma douce et tendre petite sœur.
Que Dieu t'accueille en princesse.

Ta sœur Fatima Bensalem



ባንቺ ፡ ባለችበት ፡ ኹሌም ፡ ሣቅ ፡ ጨዋታ ፣
ይሀ ፡ ነበር ፡ ከርሷጋ ፡ ኑሮ ፡ በደሰታ ።
አንድ ፡ ቀን ፡ ተነሣሽ ፡ ልብሽን ፡ አዳምጠሽ ፣
ሦስት ፡ ሩብ ፡ ዕድሜሽን ፡ በሰው ፡ ሀገር ፡
ኖረሽ ፦
*"እስቲ ፡ አኹንስ ፡ ልኺድ ፣ ወዳገሬ ፡ ልግባ ፤*
*መንገዴን ፡ ልዠምር ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ። "*
በኢትዮጵያ ፡ ጥያራ ፡ ተሳፍረሽ ፡ ኼድሽ ፣
መልካም ፡ ውጥኖችን ፡ በልብሽ ፡ ይዘሽ ።
ኑሮዬን ፡ ልለውጥ ፡ ብለሽኝ ፡ ገብተሽ ፣
ስደት ፡ ኾነብሽ ፡ ወይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስትደርሽ ፧
*"ስደት ፡ ከኾነብኝ ፡ ሀገር ፡ መመለሱ ፣*
*ለቀረኝ ፡ ማረፊያ ፡ ያምላኬ ፡ ነው ፡ መልሱ ።*
*እመነኩሳለኹ!"* ስትል ፡ ሰማኋት ፤
ይኸው ፡ ተሳካላት ፣ ጌታም ፡ ወሰዳት ።
አጎረቤት ፡ ሀገር ፡ ባለችው ፡ ከተማ ፣
ባንቺ ፡ ኼደች ፡ ዐሉ ፣ ድምፃን ፡ ሳታሰማ ።
እንዴት ፡ ብዬ ፡ ላስብ ፣ ዛለ ፡ ሰውነቴ ፤
እየተደቀነ ፡ ፈገግታሽ ፡ እፊቴ ፣
አልቀበል ፡ ዐለኝ ፣ ልቤ ፡ ተጨነቀ ፤
ዐይኔም ፡ አቀረረ ፣ አንዠቴም ፡ ታመቀ ።
*"ኀይልዬ!"* ስትዪኝ ፡ ባገኘሽኝ ፡ ቍጥር ፣
ሆዴ ፡ እየባባብኝ ፣ ልቤም ፡ ሲደነብር ፣
ያ ፡ ኹሉ ፡ ፍሥሓ ፡ ሊቀር ፡ ነው ፡ ወይ ፡ ዛሬ ፧
ምን ፡ ላድርግ ፡ ዘንድሮ ፤ ላልቅሰው ፡
አምርሬ ፤
ትንሽቱ ፡ እኅቴ ፡ ምነው ፡ ቸኰልሽብኝ ፧
እስቲ ፡ ላንሰላስልሽ ፣ ይኸው ፡ ነው ፡ የቀረኝ ።

ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ነጋ ።



Très chers amis,

Le petit jeune homme mal dégrossi que j'étais à Nancy, vers le milieu des années 70, a beaucoup appris de Mannie. Et je sais aujourd'hui qu'une part de ce que je suis devenu, doit énormément à son influence positive.

Au long de mon parcours, sans avoir toujours besoin de l'entendre de vive voix, je me suis souvent demandé ce qu'elle pouvait penser de telle ou telle de mes décisions ou positions. Son grand départ ne m'empêchera pas de l'entendre encore...

Il me reste des valeurs que j'essaie toujours de transmettre... un peu de cuisine éthiopienne aussi, pour la plus grande satisfaction de ma famille et mes amis... et puis un fort attrait pour la musique éthiopienne que j'avoue avoir encore du mal à partager autour de moi...

L'amour ne s'explique guère. Mais, après que nos routes ont divergé et que beaucoup de choses se sont estompées, alors que nous échangions, de loin en loin, par téléphone, j'ai compris que je l'aimais aussi, comme tant d'autres, parce qu'elle était aimable ; au premier sens du mot. Elle l'était si souvent, dans ses forces, comme dans ses faiblesses ! Et elle ne trichait pas !

Même lorsqu'elle se battait face à la plus rude des adversités, je ne l'ai jamais vue agir avec l'intention de faire mal. J'admirais la manière dont ce petit brin de femme parvenait à se faire respecter de chacun. Elle le faisait pourtant sans jamais se placer au dessus de son interlocuteur.

Chaque être humain était pour elle une source d'intérêt. Elle mettait naturellement à l'aise les personnes qu'elle rencontrait. Sa présence était recherchée dans tous les milieux.

J'en ai fait l'expérience aussi dans mon petit village.

Elle plaçait cependant sa famille au dessus de tout.

A 25 ans encore, Mannie manifestait le désir un peu puéril de ne jamais voir disparaître ceux qu'elle aimait. Elle déclarait vouloir partir avant eux. J'imagine que la vie s'est chargée de lui faire changer d'avis. Mais je veux croire que, quelque part, la petite fille qu'elle a su conserver en elle, n'est pas totalement fâchée de ce qui lui arrive aujourd'hui.

Transmettez, s'il vous plait, toute ma sympathie à votre maman que je crois connaître un petit peu, tant Mannie m'a parlé d'elle. Je sais que sa sagesse et sa compréhension lui étaient toujours d'un grand recours dans ses moments de doute.

Je vous embrasse très fort.

Lionel



ጥርት ፡ ባለ ፡ ውበት ፡ አምሮ ፡ የተሠራን ፡ ቁመናሽን ፡
አይተው ፥
እናት ፡ እና ፡ አባትሽ ፡ ስም ፡ አውጥተው ፡ ነበር ፡ ማናለብሽ ፡
ብለው ።

በሕይወተ ፡ *ሥጋ* ፡ ዐብረሽን ፡ እያለሽ ፥
በትልቅ ፡ ትንሹ ፡ ተወዳጅ ፡ ነበርሽ ።
ለሰው ፡ ክብር ፡ የሌለው ፡ ክፉ ፡ መልአከ ፡ ሞት ፥
*"ማን ፡ ነክቶኝ!"* የሚለው ፥
ጽጌረዳችንን ፡ ድንገት ፡ ቀጠፈብን ፥ ምንም ፡ ሳናስበው ።

ቸሩ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ፥ ለሱም ፡ የጁን ፡ ይስጠው ፤
የኛን ፡ እንደ ፡ ቀጨሽ ፥ ሞትንም ፡ ሞት ፡ ይቅጨው ።

የሚወድሽ ፡ አምላክ ፥ ወዶ ፡ የፈጠረሽ ፥
ቢወድሽ ፡ መረጠሽ ፥
ቢመርጥሽ ፡ ወሰደሽ ።
ከወዳጆቼ ፡ ጋራ ፡ በገነት ፡ ያኑርሽ!
አሜን ።

ማንዬ ፥ ማንዬ ፥
ከልጅነት ፡ ዝምሮ ፡
ጓድ ፡ ባልንጀሬ ፥
ዐብሮ ፡ አደግ ፡ ወዳጄ ፥
እንዲሁም ፡ ልበልሽ ፡
ባንቹዬ ፡ ባንቹላ ፥
መልአክ ፡ ይቀበልሽ ፡
ክንፎቹን ፡ ዘርግቶ ፥
በእልልታ ፡ በእንቢልታ ።

ከጌታችን ፡ ጋራ ፥
ቸሩ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ፡
ለዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡
አምላክ ፡ እስኪመጣ ።

ቲታ–በለጥሽ ፡ ስለሺ ።

ነሐሴ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ።
መኰንን ፡ ወዳጄነኽ ።



ክረምቱን ፡ / ፡ በጋውን ፡ አገኘን ፡ ሐዘን ፤
አለምልክት ፥  አለምናምን ፥
ደኅና ፡ የነበረች ፡ አንድ ፡ እኅት ፡ ዐጣን ።
ማጣት ፡ የሰው ፡ እንጂ ፥  መቼ ፡ የእግዜር ፡ ኾነና ፥
ማና ፡ አለብሽ ፡ ብሎ ፡ ቢሰማ ፡ ልመና ።
የሰጠ ፡ ቢነሣ ፥  አይወቀስና ፥
በሐዘን ፡ ወላፈን ፡ ተለብልበን ፡ ዓምና ፥
ላዲስ ፡ ዓመት ፡ ታርቀን ፡ ኾነናል ፡ አጣና ።

ሲወለዱ ፡ ማልቀስ ፥  ሲሞቱም ፡ መለቀስ ፥
አንዱ ፡ የደመ ፡ ነፍስ ፥  አንዱም ፡ የፍቅር ፡ መልስ ፤
ለዘላለም ፡ ሕይወት ፡ ሲወለዱ ፡ ዳግም ፥
ምነው ፡ ድምፅሽ ፡ ጠፋ ፨  እንዲያው ፡ ዝም ፣  ዝም ፤
እንዲህ ፡ ያደርጋል ፡ ወይ ፡ ገነተ ፡ ማርያም ፨

መልክን ፡ ከጣይቱ ፥  ብሩህ ፣  ቅን ፡ ውበት ፤
ባልትናን ፡ ከሥላስ ፥  ምስጉን ፡ እመቤት ፤
ምግባርን ፡ ከከፈይ ፥  ቸር ፣  ለጋስ ፣  ኂሩት ፤
አምሮን ፡ ከመስተዋት ፥  ጽሪት ፡ መጽሔት ፤
ጽድቅን ፡ ከበላይነሽ ፥  ለደክታሞች ፡ ሙት ፤
ጠባይን ፡ ከደስታ ፥  ርኅርኅት ፣  አዛኝት ፤
ማን ፡ አለብሽ ፡ ሌላ ፥  ባንቺ ፡ ውላ ፡ እናት ።

ወሌ ፡ ነጋ ።

ማናለብሽ ።

የኔ ፡ ደስታ ፡ ደስታሽ ፥  ዕመሜ ፡ ዕመምሽ ፥
የዘወትር ፡ ፈገግታሽ ፥  የጭንቅ ፡ ዕለት ፡ ሣቅሽ ፥
እምነትሽ ፡ አለቱ ፥  እማይፈራው ፡ ልብሽ ፥
እኔ ፡ አንቺ ፡ አለሽብኝ ፥  አንቺ ፡ ማናለብሽ ።

አውሳቤ ፡ ነጋ ።

በሐዘናችን ፡ ወቅት ፡ ከጐናችን ፡ ሳይለዩ ፡ ያስተዛዘኑንን ፡ ኹሉ ፥ ከቅርብም ፡ ከሩቅም ፡ የደረሱንን ፡ እና ፡ በመልእክት ፡ ያጽናኑንን ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልን ፡ እያልን ፥ ልባዊ ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀርብላቸዋለን ።

እክሮይድን ፡ ሊቋቋም ፡ ለታቀደው ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማኅበረ ፡ ምእመናን ፥ በልጃችን ፡ እና ፡ በእኅታችን ፡ በወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡ ስም ፡ የገንዘብ ፡ ርዳታችንን ፡ እናበረክታለን ። የወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡ ወዳጆችም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ማቋቋሚያ ፡ የሚውል ፡ ድጋፋቸውን ፡ ለማኅበሩ ፡ እንዲቸሩ ፡ በትሕትና ፡ እንለምናለን ። እግዚአብሔር ፡ ይስጥልን ።

የወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፡ ቤተሰብ ።

Account Name: St George Croydon Community
Account Number: 54333536
Sort Code: 23-05-80
IBAN: GB15MYMB23058054333536
SWIFT: MYMBGB2L